# የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር
# Gambella People's United Democratic Front

ሚያዝያ 18 ቀን 2000 ዓ/ም (April 26, 2008)

## ከጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር የተሰጠ መግለጫ

የጋምቤላ ክልል መንግሥት ከፍተኛ የአመራር ልዑካን ቡድን በአቶ ኡሞት ኡቦንግ የክልሉ ዋና አስተዳዳሪ የአሁኑ የካናዳ፣ የነብራስካና የሚኒሶታ ጉብኝት በአኙዋክ፣ በኑዌር፣ በመዠንገርና በኮሞ ብሔረሰቦች አባላት እንዲሰበጠር መደረጉ ከአምናው የኢሕአዴግ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር በሚኒሶታ ወያኔአዊ ተልዕኮ ጉብኝት ጋር የማይለያይ፣ የታሕሣስ 3 ቀን 1996 ዓ/ም የአኙዋክ ሕዝብ ላይ የተደረገ የጅምላ ጭፍጨፋና እልቂት ቁስል እንዲያገረሽ የሚያደርግ የከፋፍለህ ግዛ ቤተ ሙከራና የአምባገነኖች ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ተግባር በመሆኑ ከምር እናወግዛለን።

የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ጋሕአዴግ) በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ የተንሰራፋውን የወያኔ የሽብር አገዛዝ ሲታገል እነሆ አምስት ዓመታት ያስቆጠረ የፖለቲካ ድርጅት ነው። ይህ ግንባር ከሌሎች ዴሞክራሲያዊና ፍትኅ ፈላጊ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመሆን የሽብር አገዛዙን ከአገሪቱ መንግሎ ለመጣልና ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት ተባብሮ መታገሉ አማራጭ እንደሌለው ያምናል። ትግሉም ብሔራዊ አቅጣጫ እንዲይዝ ለእውነት በእውነት ለሚያምኑ፣ ትክክለኛ የባህሪ ለውጥ ለተላበሱ ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሁሉ (መጥፎ ጥሩ ሳይባል) ተባብሮ አገራቸውን ከአገዛዙ የጭቆናና የብዝበዛ መዳፍ በማላቀቅ፣ ፍትኅና ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብትና የሕግ የበላይነት የተረጋገጡባት፣ ትክክለኛ የፌዴራል ሥርዓትና አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመመሥረትና ለመገንባት ከዳር እስከዳር መንቀሳቀሱ የወቅቱ ትግል የሚጠይቀው ሃቅ ነው። ድርጅታችን ወደዚህ ድምዳሜ ሊደርስ የቻለው በብሔራዊ ደረጃ ከምርጫ 97ቱ ወዲህ ይሁን በአሁኑ ሚያዝያ ወር 2000 ዓ/ም የወረዳ፣ የቀበሌና የማሟያ የመቀጫ ምርጫ፣ የወያኔ አሸባሪ አገዛዝ የሰላማዊ ትግል ስልት አዳፍኖ በተቃዋሚ ጎራ የሚገኙት የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ሰርሥሮ በመግባት ትግሉን ማዳከሙ ብቻ ሳይሆን ነባርና አዳዲስ የፖለቲካ ድርጅቶች ብትንትናቸው እንዲወጣ አድርጓል፣ እያደረገም ነው። የለመደች እንስሳ እንዲሉ አሁን ደግሞ አምስት ዓመታት ያለው አታጋይ የጋምቤላ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት ከውሃ እንደወጣ አሣ ለማድረግ የአኙዋክ፣ የኑዌርና የመዠንገር ተወላጆች የተደራጁባቸውን የብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች አክስሜአለሁ ብሎ ከእኛ በሰረቀው አደረጃጀት ለጋምቤላ ሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም እንደቆመ በማስመሰል የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጋሕዴን) ተብሎ በተሰየመው ተለጣፊ ድርጅት ዙሪያ ካጠረቃቀመ በኋላ እነሆ አሁን ወደ ተሰደድንባቸው አካባቢዎች በመምጣት ለሕዝብ ያለውን ንቀትና የተለመደ ማን አለብኝነቱን ሊያሳየን ደፍሯል።

ይሁን እንጂ ከአኙዋክ ምሁራን የጅምላ ጭፍጨፋ በኋላ ከእልቂቱ ያመለጠውን ተጠቂ ለመርዳት ሲል ገንዘቡን ወገኖቹ በግፍ ተፈናቅለው ወደየተሰደዱበት ወደ ሱዳንና ኬንያ እየላከ ኪሱ የተራቆተበት ዲያስፖራ ጋምቤላውያን በእውነት የሚያምን ማኅበረሰብ ስለሆነ ከሌላው ሆዳምና ጥቅም አሳዳጅ ፍጡራን ጋር ትንቅንቅ ይዞ የወያኔን ደቀ መዛሙርት ለመቋቋምና ይህ የወያኔ ጎብኝ ቡድን ይቅርታ እንዲጠይቅ እንደሚያስገድድ ድርጅታችን እምነት አለው። ይልቁንም የወያኔ አሸባሪ አገዛዝ በሦስት ተከታታይ ቀናት የገደላቸውን የ424 የአኙዋክ ምሁራንን ሬሳ ቤተሰቦቻቸው በሥርዓትና በክብር እንዲቀብሩ መደረጉን፣ የሰማዕታቱ የጋራ መታሰቢያ ቀንና ቦታ በአገዛዙ ደንታ ቢስነት የተረሳ ከሆነ አክርሮ

በመጠየቅ ተለጣፊ ቡድኑ ሆነ የአገዛዙ መሪዎች ይቅርታ እንዲያሰሙ ማስገደድ ምርጫ ሳይሆን ወንድምህንና ወገንህን ከጨረሰና በግፍ ከጨፈጨፈ አካል ጋር በምን የሞራል ግዴታ ነው ጉባዔ የምትቀመጠው? ይህ ማለት በአኙዋክ ዘር ላይ የወያኔው አገዛዝ ያወጀውን የዘረኝነት ፖሊሲ አሜን ብሎ እንደመቀበል ስለሆነ ዲያስፖራው አኙዋክ ኮሙኒቲ የሞራል ግዴታውን ያላሟላ የማኅበረሰቡ ስብስብ ከወያኔ ጋር የሚመሳሰል ስለሆነ አሁንም ድርጊቱን እናወግዛለን፡፡

የጋምቤላ ክልል መንግሥት የልዑካን ቡድን ጉብኝት በዓላማው ወያኔአዊና በአገዛዙ መሪዎች አማካይነት የጀመረው የአፀፋና የንቀት ዘመቻ አካል መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የወያኔ አገዛዝ ከመልካም አስተዳደር ጋር የማይተዋወቅ፣ የሕግ የበላይነትን የሚፃረር፣ የጋምቤላም ሆነ የሌሎች ክልሎችና አካባቢዎች ጭቁን ኢትዮጵያውያንን ዕድገት የማይፈልግና የኤኮኖሚ አውታሮችን የራሱ አባላትን ኪስ ማደለቢያ ያዋለ አገዛዝ ልማት ያመጣል ብሎ መጠበቅ ከእባብ እንቁላል ርግብ ይፈለፈላል ብሎ መጠበቅ ይሆናል፡፡

ይህን የጋምቤላ ክልል መንግሥት የልዑክ ቡድንን የሰሜን አሜሪካ ጉብኝት አስመልክቶ በወያኔ ኢሕአዴግ አገዛዝ ጋምቤላ ከፀረ ሰላም ኃይሎች ጋር በተደረገው ትግል መረጋጋትና ሰላም ሰፍነዋል፣ ልማትና ዕድገት ለጋምቤላ እያስመዘገብን ነው፣ ጋምቤላና የቀረው ኢትዮጵያ በልማት ጎዳና ላይ ናቸው የሚያሰኝ ዘመቻ የሚያንፀባርቅ ሳይሆን ሦስቱ የአፍሪካ በሽታዎችን ማለት ባርነት፣ ቅኝ አገዛዝና የዘር መድሎ ፖሊሲ ሥር እንዲሰድ የሚያደርግ የቀልድ ጉብኝት ነው፡፡ ባንፃሩ ግን ጋምቤላ በልማትና በኤኮኖሚ ዕድገት ጎዳና ላይ አለመሆኑንማ ድርጅታችን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ የጋምቤላ ሕዝብ (የአኙዋክ፣ የኑዌር፣ የመዠንገር፣ የኮሞ፣ የአፑሆ እንዲሁም ከመሃልና ከሌሎች አካባቢዎች ከመጡ ወገኖች የተወለዱ) የሚመሯቸው ልማትና ኢንቬስትመንት አላቸው የሚያሰኝ አይደለም፡፡ በጋምቤላ አካባቢ ያሉት ኢንቬስተሮች በአንድ በኩል ለወያኔ አገዛዝ ካዝና ብዙ ሊያተርፉ የሚችሉትን የወያኔ ካድሬዎች በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንደተበደሩ በማስመሰል ኢንቬስተሮች ሆነው በጋምቤላ ውስጥ የሆቴል፣ የቡና ቤት፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ፣ የእርሻና የሱቅ ፈቃድ ከጋምቤላ ክልል መንግሥት እንዲሰጣቸው ተደርጎ ከኢንቬስትመንት ማናቸውም ገንዘብ ለራሳቸው ለወያኔ ቤተሰቦችና ድርጅቶች ይውላል፡፡ ዛሬ የጋምቤላ ክልል ጂዲፒም ሆነ በክልሉ ውስጥ የሚዘዋወረው የገንዘብ መጠን በጭራሽ አይታወቅም፡፡ ምክንያቱም በቀን፤ በሳምንት፣ በወርና በዓመት የሚገባው የክልሉ የገቢ መጠን በቀጥታ ወደ አገዛዙ መሄዱ ብቻ ሳይሆን የምርት ኃይሎች (ድርጅቶች) ያላቸው የክልሉ ተወላጆች ከነባር ብሔረሰቦች አኳያ ሲታይ ሚዛኑ የተዛባ እንደሆነ ይታወቃል፡፡
በሌላ በኩል ደግሞ ጋምቤላ በልማትና በዕድገት ጎዳና ላይ ነች የሚያሰኝ ምቹ ሁኔታ አለ ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ በነገራችን ላይ ስለ አካባቢና ሕዝብ ልማትና ዕድገት ስንናገር ሦስት በጣም አስፈላጊ ነገሮችን መመልከቱ ተገቢ ይመስለናል፡፡ እነርሱም፡-

1. ጤናማ ኑሮና ረዥም ሕይወት፡- ይህም የሚለካው በሕዝቡ አኗኗርና መሻሻልና የዕድሜ እርዝማኔ ነው፡፡
2. የተማረ ዜጋ፡- ይህም የሚለካው በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ከታዳጊ ወጣቶች እስከ ጎልማሶችና እስከ ከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ያለውን መሻሻል የሚመለከት ይሆናል፣
3. የተመቻቸ የኑሮ ደረጃ፡- ይህም የሚለካው በገበያ እቃዎች የመግዛት አቅምና ችሎታ ሲኖር ማለት ነው፡፡
ታዲያ ከላይ በተጠቀሱት ሦስት የሰው ልጅ የልማትና የእድገት መስፈርቶች መሠረት የጋምቤላ ክልል ሕዝብም ሆነ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁኔታ ምን እንደሆነ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ግልጽ ነው፡፡ ጋምቤላ ከቀረው የኢትዮጵያ ሁኔታ፣ ኢትዮጵያም ከዓለም ሃገሮች ተርታ ደሃ፣ ኋላ ቀርና ተረጂ ሆኖ የመገኘት ሁኔታ አጠያያቂ አይደለም፡፡
በማንኛውም አካባቢ የልማትና የዕድገት መኖር የሚገለጸው በሕዝቡ ሕይዎትና አኗኗር ላይ ሲታይ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የጋምቤላ ሕዝብ አኗኗርና ሁኔታ የሚያሳየው የሕዝቡን ሕይዎት በበጎ የሚቀይር ልማትም ሆነ እድገት እንደሌለ ነው፡፡

በተጨማሪም ለጋምቤላ ልማትና ዕድገት መኖር ዋና ነገር በትክክል የተዘረጋ ኢንፍራስትራክቸር ሲኖር ነው። ኢንፍራስትራክቸር ለሁሉም ኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ዋና የመሳቢያ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን አገዛዙ ግንዛቤ ቢኖረው መልካም ነው እንላለን።
ከላይ የጠቀስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች በጋምቤላ ክልል ባለመመቻቸታቸው የተነሳ ታንናሽ እህቶቻችን እናቶቻቸውን ለመርዳት ሲሉ ለሴተኛ አዳሪነት ሲዳረጉ፣ ወንድሞቻችን ተስፋ ቆራጮች ሆነው በአገር ቤት እራሳቸውን በመደበቅም ሆነ ተፈናቅለው በየሄዱበት ለጫትና ለአደገኛ እጽ ሱሰኛና ተገዥ መሆናቸው፣ ሌሎችም ለጎዳና ተዳዳሪነት ተዳርገውና በየአገሩ ስደተኛ ሆነው መገኘታቸውና ለስቅላትና ለሞት መዳረጋቸው የታወቀና ወገኖቻችን በየዕለቱ የሚጋፈጡት አሳዛኝ ሁኔታ ነው። ነገር ግን አገዛዙ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ብቻ በደመነፍስ የሚያካሂዳቸው የመንገድ፣ የሕንፃ፣ የአውሮፕላን ጣቢያ ማማ (ታወር) የሲቪል ኮሌጅና ትውልድ ገዳይ የሆነው የትምሕርት ፖሊሲ ዘመቻ ለጋምቤላ ሕዝብ አስተማማኝ ዕድገትና ልማት ስላልሆነ፣ እንዲሁም በውሸትና በተንኮል ላይ የተመሠረተ በጋምቤላ ምድር ያልተመዘገበና የሌለ ልማትና ዕድገት በኮምፒዩተር ፓወር ፖይንት አማካይነት ተቀናብሮ በየስብሰባው አዳራሽ እያቀረቡ ሕዝቡን ለማሳመን መሞከር ሕዝብን ለማሞኘት የሚደረግ አካሄድ መሆኑን፣ በአኳያውም ጋሕአዴግ ሁኔታውን ማጋለጥ ግዴታ ያለበት መሆኑንና ይህንን የመሰለ የውንብድና ሥራም አምርረን የምናወግዘው ተግባር መሆኑን እንገልጻለን።

የጋምቤላ ክልል መንግሥት ግልጽ የሆነ የፌዴራል መንግሥት አወቃቀርና አሠራር ምን መሆኑን አለመረዳቱ ብቻ ሳይሆን በመንግሥት ሦስት የሥልጣን ቅርንጫፎች ኃላፊነት ክፍፍል ያለው ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ብዥታ እንዳለበት ግልጽ ነው። በተለይም የጋምቤላ ክልል መንግሥት የሕግ አውጭው ምክር ቤት የመጨጫሂያ መድረክ እንጂ ሥራ አስፈጻሚውን፣ ፕሬዝዳንቱንና ኃላፊዎቹን መቆጣጠርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ ጥሩ ሕጎችን ማውጣት ያልሞከረ የወያኔ አገዛዝ የብሔረሰቦች መከፋፈል ቤተ ሙከራ ነው። በጋምቤላ ሕዝብ ላይ የሚደረገው ጭቆና፣ የቀለምና የዘር ልዩነት፣ የመረሳትና የንቀት ጦዝ፣ ክልላዊና ብሔረሰባዊ መብት፣ ባህላዊና አጠቃላይ መብቶች ጉዳይ ለውይይት ቀርቦ ሕግ የተነደፈበት ቀን ተዘግቦ እንኳን አያውቅም። በመሆኑም የጋምቤላ ክክል መንግሥት በይዘት ምንም ዓይነት የሥልጣን ክፍፍል የሌለበትና ያልተተገበረበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለፌዴራላዊ ሥርዓት ግንባታ አደገኛ ስለሆነ፣ ከአኙዋክ ምሁራን የጅምላና የግፍ ጭፍጨፋ በኋላ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በተወሰደው የአስቸኳይ ጊዚያዊ ሁኔታ የጋምቤላን ክልል መንግሥት ሥልጣንንና መብትን መነጠቁና አለመመለሱም አግባብ ባለመሆኑ ሁኔታውን እናወግዛለን።

በመጨረሻም የጋሕአዴግ ራዕይ በጋምቤላ ሕዝብ ላይ የተጫነው ማንኛውም የፖለቲካ፣ የአኮኖሚና የማኅበራዊ ጭቆና ተወግዶ፣ ሕዝቡ ሙሉ መብቶቹን እንዲጎናጸፍና የወደፊት ዕድሉ ብቸኛ ወሳኝ እንዲሆን ማስቻል ነው። ይህም የመብትና የእኩልነት፣ ትርጉም ያለውና በኢትዮጵያ ሕዝብ ፈቃድና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የፌዴራል መንግሥት አወቃቀርና አሠራር የማስገኛ ትግል የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚያደርገው ተመሳሳይ የፍትኅ፣ የእኩልነት፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ትግል ጎን ለጎንና በጋራ እንዲሆን ድርጅታችን የሚያምንበት ብቻ ሳይሆን ከምሥረታው ጀምሮ በተግባር እየተረጎመው የሚገኝ ጉዳይ ነው። የአሁኑ የጋምቤላ የክልል መንግሥት ልዑክ ቡድን ተልእኮ የጋምቤላን ሕዝብ ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ሳይሆን የወያኔን የጭቆናና የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲዎች አራማጅ በመሆኑ አጥብቀን እናወግዘዋለን።
ለሕዝባችን ብሶት ጆሮ አለመስጠትና ይባስ ብሎ ወደጠርዝ እየተገፋ መቀጠሉ የአደጋው አሳሳቢነት እንደሚባባስና ሕዝባችን እሱነቱንና መብቶቹን ለማስከበር ማንኛውንም አማራጭ ማየት እንደሚገደድ ማስጠንቀቅ እንወዳለን።

በጋምቤላ ሕዝብ ስም የሚደረገው ማጭበርበር ይቁም!

የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር